# <u>ሶስት ጥፉዎች አንድ ዕውነት አይሆኑም</u>

አሸናፊ የካናዳው

የኢትዮጵያን የፓለቲካ ሂደት የሚከታተል ሁሉ ስለ ኢሕአፓ የሚሆነውን ሁሉ ያስተውላል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከድርጅቱ በየጊዜው የሚወጡ የድሮ አባላቱ ስርዓት ለቀው የነበሩበትን እናት ድርጅታቸውን ለመናድ ሲጥሩ ብሎም ሕዝቡን ግራ ሲያጋቡት ለሚመለከት ሁሉ አሳዛኝ ነው፡፡ ያለጥርጥርም ይህ ድራማቸው ለወያኔና ለመሰል የኢትዮጵያ ጠላቶች ደስታቸው ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በጸረ ወያኔው ጎራ ሊፈጥሩት የሚፈልጉት ጨለምተኝነትና ተስፋ ለማስቆረጥ ነው፡፡ አለማወቃቸው ነው እንጅ ወያኔ ከነሱ በበለጠ ኢሕአፓ መሰረቱ የማይናጋና የሕዝብ ጠንካራ ድጋፍ ያለው መሆኑን ያውቃል፡፡ ቀለማቸው እስኪደርቅ ይጽፋሉ፣ ላንቃቸውም እስኪላቀቅ ይድክማሉ እንጅ ሕዝቡን ለማወናበድ በጭራሽ አይችሉም፡፡ የሚያበረታታው ዕውነታ ግን ድርጅቱ ይበልጥ እየተጠናከረና ፀረ ወያኔ ትግሉን እያፋፋመው ይገኛል፡፡ ለዚህ ጽሁፍ ያነሳሳኝ ዋናው ነገር ሰሞኑን "እርቀሰላም ይውረድ" የሚሉ ከድርጅቱ በተለያየ ሁኔታ የለቀቁ የድሮ አባላት የአዞ ለቅሶ በመበራከቱ ነው ሰሞኑ ደግሞ ሌላ ድራማቸው ያው የተለመደውን ውዥብር ማናፈስ ነው፡፡ በእንታረቅና ልንዋሃድ ነው በሚል ምኞት ኢሕአፓ ከትግሉ አይዘናጋም፡፡ አንባቢው በሚገባ እንዲረዳ የ"እርቀሰላም ይውረድ" አቀንቃኞቹን መሰረታዊ ማንነት ማወቁ ለግንዛቤ ያስፈልጋልና ማብራሪያ ሳላበዛ ሃቁን ብቻ ላስቀምጥ፡፡

እንደማንኛውም ድርጅት በኢሕአፓ ውስጥ በየጊዜው ተደጋጋሚ አንጃዎች ተከስተዋል፡፡ ላንጃነት ሳይበቁ በዲፐሊን ጉድለትም ድርጅቱ ያገዳቸው አባላትም ተንጸባርቀዋል፡፡ ባጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ሶስት "እርቀ ሰላም ይውረድ" የሚሉ ስብስቦች አለሁ አለሁ ሲሉ አይተናል፡፡ እነሱም

1. ኢሕአፓዴ
2. የእርምት እንቅስቃሴ
3. ትንሳኤ ኢሕአፓ

አስቲ በጥቂቱ የሚሰማኝን ልናገር፡፡

## I. <u>"ዴ"ዎች እነማን ናቸው?</u>

**ዴ** ሲሉ ዴሞክራሲያዊ ለማለት ነው፡፡ እነሱ ዴሞክራሲያዊ ሲሆኑ ጥለውት የወጡት እናት ድርጅት ኢዴሞክራሲያዊ ነው ሊሉን ነው የፈለጉት፡፡ አስቲ ስያሜው ተገቢ ስለ መሆኑ አለመሆኑ እንመርምር፡፡

**ሀ**). ይህ ቡድን በናት ድርጅቱ ስር እያለ በሚስጢር በድርጅት ላይ ቡድን ፈጥሮ ቢያንስ ካንድ አመት በላይ በሚስጢር ኣሲሯል፡፡ በደንባችን መሰረት በድርጅት ላይ ድርጅት መፍጠር ሕገ-ወጥ በመሆኑ ከድርጅት መባረርን ማስከተሉ የግድ ይሆናል፡፡ ይህ ቡድን አንጃ ለመፍጠር የወሰነው የድርጅቱ በርካታ አባላት <u>አፉዳቪት ፈርመን ከወያኔ ጋር እንስራ</u> የሚለውን ያጉብዳጆች አላማቸውን ባለመቀበላቸው ነው፡፡ አባላት ሃሳባቸውን በድምጽ ብልጫ ሲጥሉት ተገቢውን ትንተና በማቅረብ ነበር፡፡ በዲሞክራሲ ደንብ መሰረት አብላጫ ድምጽ ያገኘ ክፍል አሸናፊ ሲሆን በድምጽ የተበለጡት ደግሞ ድምጻቸውን በማሰማቸው ተደስተው ውጤቱን ግን በጸጋ መቀበል አለባቸው፡፡ ይህ የዲሞክራሲ "ሀ" እንጂ "ፖ" አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር ዲሞክራሲ 101 ነው ማለት ነው፡፡

**ለ**). ይህን ዕኩይ ተግባር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት ለማስገኘት የድርጅቱ አስቸኳይ ኮንግረስ ተጠራ፡፡ **ዴ**ዎች አባላትን በመናቅ በዚህ ኮንግረስ የሚፈልጉትን ሁሉ እናስፈጽማለን የሚል ትምክህት አይናቸውንና አእምሮአቸውን ዘግቶባቸው ነበር ወደ ስብሰባው የመጡት፡፡ ድርጅቱን ለውያኔ መታረቂያ ለማድረግ ቆርጠውና አድመው አባልም አባል ያልሆነወን ከየሜዳው አንጋግተው ወደ ጉባኤው ገቡ፡፡ ስብሰባው ተጀመረና ግንባርቀደም መሪዎቻቸው ለረጅም ሰዓት የሌለ ያልሆነውንና ያልተደረገውን ሁሉ ቀባጠሩ፡፡ አባላት በጥሞና ዝባዝንኬ ሃተታቸውን ሳይታክት አዳመጡ፡፡ ያን ሁሉ ሰዓት ፈጅተው ያቀረቡት መከራከሪያ ነጥቦች አስገመታቸው እንጅ አልፈየዳቸውም፡፡ ምላሹ ቀረበ፡፡ ሁለት ተናጋሪዎች ላጭር

ደቂቃዎች ብቻ መልስ ሰጡ፡፡ ዕውነት ከጎናቸው ስለነበር መልሳቸው ግልጽና አጭር ነበር፡፡ ቤቱ ማለትም አባላቱ ውይይት ልክ ሲጀምር ዴዎች ያልጠበቁት ሽንፈት ሲሸታቸው እንደሚሊሻ ተንጋግተው ወጡ፡፡ ጉባኤውን ረገጡ፡፡

**ሐ**). ዴዎች ሲፈረጥጡ እንደ ወንበዴ ዘቅጠው ነበር፡፡ የተኙበትን የሆቴል ወጭና የምግብ እዳ በድርጅቱ ላይ ጭነው በቀጣፊንተ ነጎዱ፡፡ ከፈልንም ለማለት በባንክ ገንዘብ የሌለው ቼክ ጻፉልን፡፡ ቼካቸው ከባንካቸውን በር ተጋጭቶ ተመለሰ፡፡ ይህ ደግሞ የሞራል መዝቀጥ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል፡፡ ሌቦች ማለቱ ስለከበደኝ ነው፡፡

**መ**). ሕገወጥ በሆነ መንገድ የድርጅቱን ስም፣ ዓርማና ልሳኑን ዲሞክራሲያ ያለ ሃፍረት መጠቀም ቀጠሉ፡፡ የነሀለሉ መግለጫዎችን አወጡ፡፡ ጠላትን አስደሰቱ ሕዝቡን አሳዘኑት፡፡ ኢሕአፓ ተከፋፈለ የሚለውን መልእክታቸውን አገር ቤት ባለ የወያኔ ጋዜጣ ላይ እወጡ፡፡ በየጠላት ዜና ማሰራጫዎች እየቀረቡ ድርጅቱን ሰይጣን አደረጉት፡፡ ደከሙ፣ ደከሙ በከንቱ፡፡ ሕዝብ ጆሮ ነሳቸው፡፡

**የሆነውስ ሆነ ግን ዛሬ ዴዎች የት ደረሱ? ወዴትስ እያሽቆለቆሉ ነው?**

ዛሬ ያሉት ዘቅጠው ወርደው ለመሸሸጊያ ብለው “የሽግግር ጉባኤ” ውስጥ ተደብቀዋል፡፡ ፓርላማ መሆኑ ነው፡፡ አመት ሳያስቆጥሩ ዴዎች መባላት ጀመሩ፡፡ ዲሲፕሊን አጉድላችኃል ተብለው አራት አምስት ሰዎች ተባረሩ፡፡ አንዳንድ  አጠቃላይ ሁኔታው ያልገባቸው አባሎቻቸውም ሾልከው ወጡ፡፡ ኪሳራ በኪሳራ፡፡ ነገራቸው ሁሉ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ሆኖባቸው ያኔ ሊንዱት የነበረውን ድርጅታቸውን እንታረቅና እንገንባው ከሚል አዙሪት ላይ ወደቁ፡፡ ዴዎች አንድ የሳቱት ነገር ደግሞ አላቸው፡፡ በሽግግር ሸንጎ ውስጥ ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡ እንደው እንበልና <u>ሰማይና ምድር ተገለባብጠው</u> ኢሕአፓና ዴዎች ቢስማሙ ስለ ሸንጎው ጉዳይ ምን ያደርጉ ይሁን? ያኔ እኛን እንደከዱ ሸንጎውንም ይከዱ ይሆን ወይስ እኛን አስገድደው የሸንጎ አባል ሊያደርጉ?




ለመሆኑ ዴዎች ስለፈጸሙት በርካታ ስህተቶች ተሳስተናል ሲሉ የተሰሙበት ጊዜ አለን? በፍጹም!

## II. <u>የእርምት ንቅናቄ</u>

እነኚዎች ደግሞ እርምት የሚለው ምች የመታቸው ከሜዳ ጀምሮ ነው፡፡ ስለ ሰራዊቱ እንጅ ስለ ከተማወ አይደለም እርምት መኖር አለበት የሚሉት፡፡ ያኔ እነ ታምራት ላይኔ እርማት ለማድረግ ፈልገው ነበር ብለው ይጀምራሉ፡፡ ታምራትማ እርማቱን ትቶ ወያኔ ሆነ፡፡ ዘመንተኞቹ አምስት ግልሰቦች ደግሞ “የድርጅቱ ሕግ ተጥሷል፡፡” በማለት ጠብ ያለሽ ጀመሩ፡፡ ሕግ እናስከብራለን ባዮቹ ሕግ አፍርሰው ምሳቸውን  እንደ ዴዎቹ በድምጽ ብልጫ አያምኑም፡፡ እንደ ዴዎቹ እነሱም ከአመራር አባላት ጋር የማያስማማ ዛር አለባቸው፡፡ <u>ገና አላምጬ አልዋጥኩትም እንጂ ይህ ስብስብ ሁሉም ባይሆን የዘር ልጉዋም በስተርጅና እየጎተታቸው እንደሆን የማይናቅ ሹክሹክታ ይሰማል</u>፡፡ ዕውነት ከሆነ ሞረሹ ማለት ነዋ፡፡

ላንጃነት ባያንሱም ግን ከጊዜ መጣበብ ወይም ድርጅቱ ቀድሞ በመንቃቱ ይህን የሳሳ ጥርቅም በዲስፕሊን መጣስ እንዲገለሉ ተደርገዋል፡፡ እንደስብስብ ሳይሆን በነጠላነት፡፡ በዲስፕሊን የተባረረ ወደ ድርጅቱ ለመመለስ ከፈለገ አመክሮው መታየት ይኖርበታል፡፡ ግለሰቦቹ የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል እንጅ የድርድር ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም፡፡ እስከ ጽህፈት ቤት ሰበራና አጸያፊ ስድብና ለመደባበብም መቃጣት የዚህ ስብስብ አንዱ አስከፊ ባህሪው ነው ፡፡ ለነገሩ በዚህ ወገን ያሉት ጸረ- አንጃ እንደነበሩ መስካሪ ነኝ፡፡




ባለ እርምቶቹ ሌላውን ለማረም ከመከጀላቸው በፊት ስህተታቸውን አምነው ለእርምት መዘጋጀት አለባቸው

## III. <u>ትንሳኤ ኢሕአፓ</u>

ስለ ትንሳኤዎች ብዙም ባላውቅም አንድ ቃለ መጠይቅና ቁጥር ሁለት መግለጫቸውን አንብቤአለሁ፡፡ ቀደም ሲል ከዴዎቹ ጋር ከድተውን የወጡ ሲሆኑ ከዴዎቹም ይባረሩ ወይም በፈቃዳቸው ስለመውጣታቸውን በውል አላውቅም፡፡ ጥሪያቸው ባንድ ወቅት ኢሕአፓ የነበሩና አሁን ድርጅቱን የተውትን ሁሉ ነው የሚጋብዘው፡፡ በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱት ሁሉ ልመለስ ካለ ትንሳኤውች ያስተናግዱታል ማለት ይመስለኛል፡፡ ከታማኝ ምንጭ እንደተረዳሁት ከሆነ የእርቀሰላሙ መሪ አስተናጋጅ መሆን ስለሚፈልጉ ምናልባት አብሮ የመራመድ ችግር ከወዲሁኑ ሊደቀንባቸው ይችል ይሆናል፡፡



ልክ እንደ አንጃዎቹ ትንሳኤዎቹም አንድም ስፍራ ተሳስተን ነበር የሚል ጸጸት አልጎበኛቸውም፡፡

<u>ቁልፍ የሆነውን ***መተማመን*** በምን ሁኔታ ሁለቱም ወገን ያስተናግዱት ይሆን??????</u>

ያንድ ድርጅት መሰረቱ በአባሎች መካከል ያለው መተማመን ነው፡፡ ኢሕአፓን ላለፉት 42 አመታት አጠንክሮ ያቆየው በአባላት መካከል ያለው መተማመን ነው፡፡ ይህ መተማመን ሲጠፋ ድርጅት ይታወካል ችግሩን እስኪፈታ ድረስ፡፡

ከድርጅቱ ባንጃነትም ይሁን በመታገድ ሲለዩ ስልጣኔ ባጣ መልኩ አውግዘውናል፣ ሰይጣን አድርገውናል፣ ኢዲሞክራሲያውያን አድርገውናል፣ ለውጥ አንጋች ብለውናል፣ ለመሆኑ አዳማጭ አጡ እንጂ ምን ያላሉን ነገር አለ? አሳፋሪው ነገር ደግሞ ኢሕአፓን ከሚጠሉ ሚዲያዎች ዘው ብለው ታሪካችንን ሲያበላሹ ከርመዋል፡፡ አሁንም አላቆሙም፡፡ አና እንዴት ተማምነን ነው ፡-

*1ኛ. ዕርቀሰላም ማውረድ የሚቻለው*

*2ኛ. ምናልባት ያልጨረሱት (ያላጠናቀቁት) የማፍረስ ተልዕኮ ስላልተጠናቀቀ እንደገና ተቀላቅለውን ሊያጠፉን ይሆን?*

*3ኛ. ዳግመኛስ ላይከዱኝና ጥቃት ላይፈጽሙብን ምን የሚያስተማምን ዋስትና ሊሰጡን ይችላሉ?*

*4ኛ. ብንስማማና አንድ ላይ መስራት ስንጀምር እንዴት ተደርጎ ነው በነፃ አእምሮ መግባባት የምንችለው?*

የዕርቁ ሰላሙ አያያዝ በራሱ ከፍተኛ ችግር አለበት፡፡ ምክንያቱም ኢሕኣፓ ባንድ ጊዜ ከሶስት ባላንጣዎቹ ጋር መነጋገር አይቻለውምና፡፡ አንዱ አገር ቤት ገብተን መታገል አለብን የሚል የፓሊሲ ለውጥ ያለው ነው፡፡ ሁለተኛው ያልተሰበረን ሕግ መጠገን ይፈልጋል፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ማንም ይሁን ማንም ብቻ መምጣት ከፈለገ የድሮ ኢሕአፓ አባላትን መቀበል አለብን የሚል ነው፡፡ ሶስቱም የራሳቸውን ዕርቀሰላም ማውረድ በቅድሚያ የሚጠበቅባቸው ይመስለኛል ከኢ ሕ አ ፓ ለመታረቅ ከማሰባቸው በፊት፡፡

ሌላው ችግረ ደግሞ ባስታራቂነት የተሰየሙት ሽማግሌዎች ሁኔታ ነው፡፡ ባስታራቂነት የሚሰየሙት ሰዎች በሁለቱም ወገኖች የተመረጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሁለቱም ወገኖች የሚያከብሩአቸው ግለሰቦች ሊሆኑ ይገባል፡፡ አንዱ ወገን ያልፈቀደው ሽማግሌ ለሽምግልናው መሳካት አይጠቅምም፡፡ ሽማግሌዎች አድሎአዊ ሊሆኑ አይጠበቅባቸውም፡፡ በተለይ ደግሞ በድርጅ መታቀፍ የለባቸውም፡፡ ለዚህ ነው የሽማግሌዎቹ ቅንብር ከችግር ፈችነት ወደ ችግር ቀፍቃፊነት መሸጋገር እንዳይገባው ጥንቃቄ ማድረግ አለብን የምንለው፡፡

ሌላው ታላቅ ችግር ደግሞ ከትግል የመዘናጋቱ አደጋ ነው፡፡ኢ ሕ አ ፓ ታላቅ የሆነ ሕዝባዊ ሃላፊነት አለበት፡፡ የኢ ሕ አ ፓ ዋነኛው ትኩረቱ ወያኔን መታገል እንጅ እዚያም እዚህ አንድ ወቅት ላይ ኢ ሕ አ ፓ ነበርኩ ከሚሉ ጋር ለእርቀሰላም መድከም አይደለም፡፡ ለነገሩ የወያኔ አንዱ ዓላማው የቆራጥ ታጋዮችን ሂደት ማደናቅፍ በመሆኑ አዘናጊዎችን በገንዘብና በስልጣን መስጠት እንደሚያባብላቸውና እንደሚያሰራቸው ጸሃይ የሞቀው ሃቅ ነው፡፡

ሊሆን የሚችለውን ልገምት፡-

**አንድ** - ሶስቱም እንደሚመኙት ያለቅድመ ሁኔታ በቃ እንታረቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለኢሕአፓ አባላት በግርድፉ የሚዋጥ አይሆንም፡፡ አባባሉም በራሱ ፍርደ ገምድል ነው፡፡

**ሁለት**- ባንዳነት ተሰልፈው በተለይም የድርጅቱን መሰረታዊ ዓላማ (ፕሪንሲፐል) ለመለወጥ በመነሳት ከድርጅቱ ጋር ከማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ ተገብቷል፡፡ እርቀሰላም ለማድረግ በመጀመሪያ ግለሂስ በግለሰባ ደረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡ በዲስፕሊን ጉድለት የተባረሩት ደግሞ ማድረግ ያለባቸው ያጎደሉትን ሕግ አምነው የይቅርታ ደብዳቤ በግለሰብ ደረጃ ማስገባት አለባቸው

**ሶስት**፡- የሶስቱ መንገድ ከኢሕ ኣፓ እጅግ በጣም የሚለይ በመሆኑ ያላቸው አማራጭ ሶስቱም ማለትም ዴዎች፣ አምቶችና ትንሳኤዎች መሰረታዊ ልዩነት ስለሌላቸው ህደት መፍጠር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር አለባቸው፡፡ይህ ግን መልካም የሚሆነው ኢሕአፓ የሚለውን ስያሜ ለባለቤቱ ትተው መሆን አለበት፡፡ ሌላ ስም ፍጠሩ፡፡

ባጭሩ

እነዚህ ውዥንብር ፈጣሪዎች አደብ መግዛት ከቻሉ የትግላቸውን ጦር በኢሕ አፓ ላይ ከማነጣጠር ይልቅ ወደ ወያኔ ያዙረት፡፡ ከወያኔ ለመዋጋት ካልፈለጉ መብታቸው ሲሆን ከኢህ አፓ ጋር የገጠማችሁት ጦርነት አይበጃችሁም፡፡ ምክር የምትሰሙ ከሆነ የድርጅቱን ስምና ልሳኑን ልቀቁ፡፡ የተንሸዋረረ ዓላም ይዛችሁ ኢሕ አፓ የሚለውን ስም ለመጋራት አትሞክሩ፡፡ ስሙም ልሳኑም ልካችሁ አይደለም፡፡ ይሰፋባችኃል፡፡ ለአላማችሁና ለተግባራችሁ የሚመጥናችሁ ስምና ልሳን ተትረፍርፎ በምድረ አሜሪካ ታገኛላችሁ፡፡ በዚህ በጠራችሁት ስብሰባ ላይ አንሱና ተነገሩ፡፡ አዲስ ስምና ልሳን ይዛችሁ ስትወጡ ከሚደግፉችሁ ቀዳሚ እሆናለሁ፡፡